# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**<u>አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስብሰባ</u>**

አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስብሰባ ዛሬ በ4/28/19 ከመደበኛው የአምልኮ ፕሮግራም በኋላ ይኖረናል። በዚህ ስብሰባ በ2018 የተፈጸሙ አንዳንድ ክንውኖችና የፍይናንስ ሁኔታን እንመለከተታለን። እደዚሁም አጠቃላይ የውይይት ጊዜ ይኖረናል። አባላት ሁሉ በዚህ ፕሮግራም ላይ እንድንገኝ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።

**በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት**

- ቀን፡ 7/4 - 7/6/2019
- ስልክ፡ (920) 294-3323 Booking ID number= 14589 or Yemsrach
- በዚህ ፕሮግራም ፓስተር አሳየኸኝ በርሄ ያገለግለናል።
- እሳካሁን 58 አዋቂዎችና 60 ልጆች ተመዝግበዋል። ሪዘርቭ ያደረግናቸውን ክፍሎችን በMay 3 ስለምንለቅ ያልተመዘገባችሁ ተመዝገቡ።
- በዚህ ፕሮግራም ጨዋታዎችን በማቀድና በማስተባበር ለማገልግል የምትፈልጉ ስማችሁን ለረድኤቱ እንድትሰጡ እንጠይቃለን።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም።"
(ማቴ. 28:6)

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m. |
|---|---|
| **April 28, 2019** | **ሚያዚያ 20፤ 2011 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት ................. እህት ሰናይት ከበደ

አምልኮ....................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ .......... ወንድም ጻደቀ ጴጥሮስ

ቃል ............. ወንድም ጌቱ ጳውሎስ

ማጠቃለያ ................. ፕሮግራም መሪ

የቤተ ክርስቲያን አባላት ስብሰባ ..... ወንድም ሲሳይ መሸሻ

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል።”

(ዮሐ. 11:25)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| **መሪ** | **ቀን** | **አድራሻ** |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ትንሳኤና ሕይወት ክርስቶስ ነው።

*“ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል።” (ዮሐ. 11:25)*

ትንሳኤ ድል ነው። ትንሳኤ ዳቢሎስ የተዋረደበት ድል ነው። ትንሳኤ የሞትና የሲኦል ሃይል ተሽሮ ሕይወት የነገሰበት ድል ነው። ትንሳኤ ጨላማ በብረሃን የተሻረበት ድል ነው። ትንሳኤ የሰው የኃጢያት ዋጋ ተከፍሎ ክርቶስን የተቀበሉና በስሙ ያመኑ ሁሉ የክርስቶስን ሕይወት የተካፈሉበትና የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑበት ድል ነው። ትንሳኤ የእግዚአብሔር የብርታቱ ጉልበት የተገለጠበት ድል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ሲነሳ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ። (ኤፌ. 1:20-21) የእግዚአብሔር ቀኝ የሃይልና የድል ስፍራ ነው። ይህ ስፍራ ክርስቶስ በድል ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይ ሆኖ የተቀመጠበት ስፍራ ነው። ይህ ስፍራ ክርስቶስ በሰማይና በምድር ሁሉ አሁንና ለዘላለም ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ ከፍ ብሎ በድል የተቀመጠበት ስፍራ ነው። ትንሳኤ ክርስቶስ አለ ልክ ከፍ ከፍ ያለበት ነው። (ፊሊ. 2:9) ከዚህም የተነሳ በሰማይና በምድር ያለ ስም ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከካል። መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክራል። (ፊሊ. 2፡ 10-11)

ትንሳኤ ክርስቶስ ነው። በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ነው የሞትና የፍረሃት ቀንበር የተሻረልን። እርሱ ሞታችንን ሞቶ በትንሳኤው በሞት ላይ ስልጣን የነበረውን ዳቢሎስን ሻረው። በትንሳኤው ሃይል ወደ ክብር አመጣን። አዲስ ሕይወት እንድናገኝ ያደረገን ትንሳኤው ነው። አልዓዛርን ከመቃብር የጠራው ጌታ እኛንም በትንሳኤው ኃይል ከመቃብራችን አውጥቶ በህይወት ኑሩ አለን። ስለዚህ ኢየሱስ ከሙታን ስለትነሳ እኛም ደግሞ በትንሳኤ ኃይል እንድንኖር የትንሳኤ መንፈስ ተሰጠን። አሁን በኛ ውስጥ ያለውና በኛ የሚሰራው መንፈስ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳው የትንሳኤ መንፈስ ነው። ያ መንፈስ አሁን ለመንፈሳችን ትንሳኤን ሰጥቶታል። ለስጋችን ደግሞ የትንሳኤን ተስፋ አቀዳጅቶታል።

ትንሳኤ ታላቅ ነገር ስለሆነ ሁልጊዜ ጠላትን ያስደነግጠዋል። ክርስቶስ ተነስቶ መቃብሩ ባዶ በሆነ ጊዜ ዳያቢሎስ አናቱ ተመታ። ስለዚህም ኢየሱስ አልተነሳም ብላችሁ ዋሹ የሚል የውሸትን ድሪቶ ሰፋ። “እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት” ብላችሁ አስወሩ አለ። (ማቴ. 28:13) ስለዚህ ውሸት ትንሿ ልጇ በመገረም ዳዲ “ተኝተው ከሆነ እንዴት ተሰረቀ ለማለት ይችላሉ፤ የተኛ እንዴት የሚሆነውን ያውቃል” ብላ እንደታዘበችው ውሸቱ ለሕጻን እንኳ ስሜት የማይሰጥ ነበር። ነገር ግን የትንሳኤው ሃይል አሸንፎአል። ወሸት እውነትን ሊከድን አይችልምና፤ ጨላማም ብረሃንን ለመጋረድ አቅም የለውምና። ወገኖቼ፡- ኢየሱስ ተነስቷል። ለብዙዎችም ከትንሳኤው በኋላ ታይቷል። ለኛም ደግሞ ይህ የትንሳኤ ጌታ ተገልጦልናል፣ በርቶልናል። ኢየሱስ ከሙታን በመነሳቱም መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናል። ዛሬ ትንሳኤውን በትንሳኤው ኃይል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እናውጃለን። ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ ተነሳ፤ እኛንም አስነሳ። አሜን!